# የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## መመሪያ ቁጥር 165/2017

## የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የአገልግሎትና ድጋፍ ማዕቀፍ

# የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የአገልግሎትና ድጋፍ ማእቀፍ መመሪያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአምራች ኢንዱስትሪ ንዑሳን ዘርፎች ላይ በማተኮር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ዘርፈ ብዙ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ማዕቀፎችን በመቅረፅና ተግባራዊ በማድረግ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠርና እና ለሀገራችንና ለከተማችን ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ማበርከት ማስቻሉ፤

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የዕድገት ደረጃና ፍላጎት መሰረት ያደረገ ድጋፍ በመስጠት፣ ጥራትና ምርታማነታቸውን በማሻሻል ተወዳዳሪና ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ በማስፈለጉ፣ በሚደረግላቸው ድጋፍ እና በሚያከናውኑት የምርታማነት እድገት መሰረት የላቀ የዕድገት ደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ድጋፍ በማድረግ የማያቋርጥ የኢንዱስትሪ እድገት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በተጨማሪም ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊ በመሆኑ እና የላቀ የዕድገት ደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ በማስፈለጉ፣

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የእድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችንና በድጋፍ ማዕቀፍ አተገባበር ሂደት የሚታዩ ችግሮችን ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት መፍታት በማስፈለጉ፤

ጥራትና ምርታማነታቸው እንዲሳለጥ ለማድረግ የካይዘን አሰራርን በውጤታማነት ተግባራዊ ማድረግ ለኢንዱስትሪው የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ በአሰራር እና ህግ ማእቀፍ መደገፍ የሚገባ በመሆኑ፤

የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነትና ውጤታማነትን ለማሳደግ፣ ያለውን ውስን ሃብት በፍትሃዊነት፣ በአሳታፊነት እና በተወዳዳሪነት መንፈስ ግልፅ አሰራር በመዘርጋት መተግበር በማስፈለጉ፤

ቀደም ሲል ሥራ ላይ የነበረው የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ቁጥር 152/2016 ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶችን በማረም እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል በአዲስ መመሪያ መተካት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 ዓ.ም አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ቁጥር 165/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
   2. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
   3. **"ቢሮ"** ማለት የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤
   4. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት የክፍለ ከተማ የኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ነው፤
   5. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአስተዳደሩ የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤንጀሲ ነው፤
   6. **"አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት ማሽን፣ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል ግብዓት በመጠቀም የማምረት ሂደት ውስጥ ያለና ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤
   7. **"ተኪ ምርት"** ማለት በስትራቴጂው እንደተቀመጠው ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶችን በተመሳሳይ ጥራት በሀገር ውስጥ የሚመረት ምርት ነው፤
   8. **"አንቀሳቃሽ"** ማለት በአነስተኛ፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ባለ አምራች ኢንዱስትሪ ተደራጅቶ በማምረት፤ ምርትን በመሸጥ ወይም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማሩ የአምራች ኢንዱስትሪ አባላት ናቸው፤
   9. **"ክላስተር"** ማለት በአንድ ለተወሰነ አካባቢ ሁለትና ከዚያ በላይ የተገነቡ መስሪያ ቦታዎች ሆነው ተመጋጋቢ ምርቶችን የሚመረቱበት፣ የሚሸጡበትና አገልግሎት የሚሰጡበት የመስሪያ ቦታዎች ስብስብ ነው፤
   10. **"ጥቃቅን አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት የአምራች ኢንዱስትሪውን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ እስከ አስር ሰዎች በስራ ላይ የሚያሰማራ እና

የጠቅላላ ሀብቱ መጠን እስከ ብር 600,000 (ስድስት መቶ ሺ.ህ) ያለው አምራች ኢንዱስትሪ ነው፤

11."**አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪ**" ማለት የአምራች ኢንዱስትሪውን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከአስራ አንድ እስከ ሃምሳ ሰዎች በስራ ላይ የሚያሰማራና የጠቅላላ ሀብት መጠን ከብር 600,001 (ስድስት መቶ ሺ.ህ አንድ) እስከ 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ያለው አምራች ኢንዱስትሪ ነው፤

12."**መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ**" ማለት የአምራች ኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከሃምሳ አንድ እስከ አንድ መቶ ሰዎች በስራ ላይ የሚያሰማራና የጠቅላላ ሀብት መጠን ከብር 10,000,001 (አስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) አምራች ኢንዱስትሪ ነው፤

13."**ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ**" ማለት ከ100 (መቶ) በላይ ቋሚ ሰራተኛ የያዘ እና ከ90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) በላይ ጠቅላላ ሀብት ያለው አምራች ኢንዱስትሪ ነው፤

14."**የዕድገት ደረጃ**" ማለት በአነስተኛ ወይም መካከለኛ ወይም በከፍተኛ የአምራች ኢንዱስት ዘርፍ የተሰማሩትን የሚመለከት ነው፤

15."**የዕድገት ደረጃ ሽግግር**" ማለት አንድ የአምራች ኢንዱስትሪ በዕድገት ደረጃው የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ ዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት መሸጋገርን የሚመለከት ነው፤

16."**የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት ዕድሳት**" ማለት በአነስተኛ ወይም በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርተው ላሉ አምራቾች በአመት አንድ ጊዜ በዘርፉ ውስጥ በስራ ላይ ስለመሆናቸው በመስፈርቱ መሰረት ታይቶ የሚሰጥ ሠርተፍኬት ነው፤

17."**ቋሚ የሥራ ዕድል**" ማለት በማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከስልሳ ቀናት ያላነሰ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በደመወዝ ክፍያ ሰነድ የተረጋገጠ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው፤

18."**ጊዜያዊ የሥራ ዕድል**" ማለት በማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ከስልሳ ቀናት ያነሰ ጊዜ ክፍያ በማግኘት ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው፤

19. **"የገበያ ትስስር"** ማለት ለአንድ አምራች ኢንዱስትሪ የገበያ ዕድል መፍጠር ከመንግስት ተቋማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥና ውጪ ከሚገኙ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት በጎንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት የሚፈጠር የግብይት ወይም የሥራ ትስስር ነው፤

20. **"የማምረት አቅም አጠቃቀም"** ማለት በአንድ አገር ወይም በድርጅት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ ሀብቶችን የሚያመላክት ሲሆን አገሪቱ ወይም ድርጅቱ ምንም እጥረት ሳይፈጠር ማምረት ከሚችለው ሊደረስበት የሚችል የምርት መጠን ያመረተውን እና አሁናዊ የምርት መጠን በማስላት የሚገለፅ ነው፤

21. **"ምርታማነት"** ማለት ውሱን ግብዓትን በውጤታማነትና በብቃት ተጠቅሞ በማምረት አሰራር የምርት ጥራትና ብዛትን ማሳደግ ነው፤

22. **"የሰራተኛ እና የስራ ላይ ደህንነት"** ማለት በምርት ሂደት በመሰሪያ ቦታው እና በሰራተኛው ላይ ከሚደርስ ማንኛውም አደጋ የመጠበቅ ሁኔታ ነው፤

23. **"የዘርፍ ማህበራት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ"** ማለት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እና ንዑስ ዘርፍ በንግድ ህጉ ከተደራጀ አምራች ኢንዱስትሪ ከክፍለ ከተማ እስከ ማዕከል የማህበሩ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው የአመራር ስራ የሚሰራ አካል ማ ለ ት ነው፤

24. **"ጠቅላላ ሃብት "** ማለት የአንድ አምራች ኢንዱስትሪ የተከፈለ እና በብድር የተገኘ ሃብት ነው፤

25. **"የተጣራ ካፒታል"** ማለት የአንድ አምራች ኢንዱስትሪ ጠቅላላ ሃብት ሲቀነስ ዕዳ ነው፤

26. **"የምርት ወይም የአገልግሎት ማስተዋወቂያ ዘዴዎች"** ማለት ምርትን ወይም አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቂያ መንገድ ነው፤

27. **"ገበያ"** ማለት በአካባቢ፣ በክልልና በውጪ ሀገር ደረጃ የሚገኝና የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት በዋጋ ተወዳዳሪ ሆነው የሚቀርቡበት ነው፤

28. **"ግብይት"** ማለት በሻጭ እና በገዥ መካከል የሚካሄድ የምርትና አገልግሎት ልውውጥ ማለት ነው፤

29. **"ንዑስ ስራ ተቋራጭነት"** ማለት የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወይም የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመለየት ሥራውን በከፊል

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሰራ ውል በመፈጸም የሚካሄድ የግብይት ሥርዓት ነው፤

30. "**አውትሶርሲንግ**" ማለት በመንግስታዊ፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና ኩባንያዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚቀርብበት የግብይት ሥርዓት ነው፤

31. "**ፍራንቻይዚንግ**" ማለት በተወሰኑ ለየት ባሉ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከአምራቹ ጋር የንግድ ስምምነት ውል በመፈጸም በውሉ መሰረት በውል ሰጪው የንግድ ስም፤ምልክትና ፈቃድ ለመስራት የሚያስችል የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፤

32. "**አውትግሮወር**" ማለት በአግሮ - ፕሮሰሲንግ ሥራ ላይ የተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጓቸውን የግብርና ግብዓቶች በኢንተርፕራይዞች ተመርቶ ወይም እሴት ተጨምሮበት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በሚደረግ ስምምነት ውል በመፈጸም የሚቀርብበት የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፤

33. "**የገበያ ዳይሬክተሪ**" ማለት የአምራች ኢንዱስትሪዎች አድራሻ መረጃ የምናስተዋውቅበት የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው፤

34. "**ኢ-ኮሜርስ**" ማለት አምራች ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ድረ ገጾችን በመክፈት ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት የግብይት መሳሪያ ነው፤

35. "**ጥሬ ዕቃ**" ማለት አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የምንጠቀምበት ግብዓት ነው፤

36. "**ካታሎግ**" ማለት አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን በዝርዝር በህትመት በፎቶግራፍ በማስደገፍ ምርትና የምርት ናሙናቸውን የሚያስተዋውቁበት መሳሪያ ነው፤

37. "**ማምረት**" ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው እቃ ማግኘት ነው፤

38. "**ከይዘን**" ማለት የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ አስተሳሰብና መሣሪያ ነው፤

39. **"የካይዘን ሥልጠና አገልግሎት"** ማለት አምራች ኢንዱስትሪዎች ጥራትና ምርታማነታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል የካይዘን አስተሳሰብና መሣሪያ ለመረዳትና ለመተግበር የሚያስችል የሥልጠና አገልግሎት ነው፤

40. **"የካይዘን ትግበራ እና ማማከር አገልግሎት"** ማለት አምራች ኢንዱስትሪዎች የሥራ ቦታዎችን ምቹ እንዲያደርጉ፣ ተቋማዊ የማሻሻያ ሥርዓት እንዲዘረጉ፣ ጥራትና ምርታማነታቸውን እንዲያሻሽሉ በጥራት ቁጥጥር ቡድኖች በቡድን የመስራትና የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግር በባለቤትነት መንፈስ እንዲፈቱ፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ተግባራዊ በማድረግ ወደ የማያቋርጥ የማሻሻያ ዑደት እንዲገቡ እና ትግበራው ተቋማዊ እንዲሆን የማማከር እና የትግበራ ክትትል ሥርዓት ነው፤

41. **"የምርት ጥራት"** ማለት የደንበኞችን ግምት የሚያሟላ ወይም የላቀ የምርት አገልግሎት ደረጃ እና የምርቱን አጠቃላይ የላቂነት መለኪያ የሚያመላክት ነው፤

42. **"የካይዘን አማካሪ"** ማለት አምራች ኢንዱስትሪን ስለ ከይዘን አስተሳሰብና መሣሪያዎች ለማሰልጠንና ለማማከር ብቁ የሆነ ሰው ነው፡፡

43. **"የካይዘን ልማት ቡድን "** ማለት የካይዘን አመራር ፍልስፍናን ለማወቅ፣ ለማስረጽ እና ቀጣይነት ያለው የጥራትና ምርታማነት ሥራዎችን ለመከወን፤ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች የቡድን አባል በመሆን የሚሰሩበት በአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈጠር አደረጃጀት ነው፤

44. **"ከይዘን ተግባሪ ተቋም"** ማለት በኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ድጋፍና ክትትል የሚደረግላቸው በከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ የእድገት ደረጃ የሚገኙ የአምራች ኢንዱስትሪ ተቋማት ማለት ነው፤

45. **"ከይዘን አስተግባሪ ተቋም"** ማለት በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ሰፊና የማያቋርጥ የጥራትና ማሻሻያ ሥራዎችን በማከናወንና እንዲተገበር በማድረግ በከተማ አስተዳደሩ ሥር የሚገኙ የአምራች ኢንዱስትሪ ተቋማትን ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ስልጣን የተሰጠው የኢንድስትሪ ልማት ቢሮና በስሩ ያሉ አደረጃጀቶችን የሚያካትት ተቋም ነው፤

46. **"የካይዘን ትግበራ ጥራት ማረጋገጥ"** ማለት ከይዘንን የሚተገብሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በተቀመጠው የትግበራ ስታንዳርድ ወይም ደረጃ መሠረት መተግበራቸውን በየደረጃው በማረጋገጥ የማስተካከያ ስራ መሥራት ነው፤

47.**"እውቅናና ማበረታቻ"** ማለት አምራች ኢንዱስትሪ ቀጣይነት ያለውና የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ፣ አዳዲስ ፈጠራና የተሻለ ሐሳብ ለማመንጨትና ለማበረታታት በካይዘን ሥልጠና እና ማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው በምዘና የላቀ አፈፃፀም ለሚያሳዩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሠጥ የጥራት እውቅና ምልክት ነው፤

48.**"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ምርት ለማምረት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን ሲሆን አክሰሰሪዎችን ይጨምራል፤

49.**"የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ"** ማለት የፋይናንስ ኪራይና የዱቤ ግዥን ያጠቃልላል፡፡

50.**"አቅራቢ"** ማለት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ አምርተው ወይም ከውጭ ሀገር አስገብተው የሚሸጡ ተቋማት ናቸው፡፡

51.**"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

52.በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቢሮው፣ በጽህፈት ቤቶች እና በአነስተኛ፣ በመካካለኛ እና በከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የእድገት ደረጃን እና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ በመስጠት የምርት ጥራትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ ለከተማው የኢኮኖሚ እድገት፣ የስራ ዕድል ፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የላቀ አስተዋጾ ማበርከት ነው፡፡

## 5. የመመሪያው መርሆዎች

1. በአሳታፊነትና በፍትሀዊነት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤
2. ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፤
3. ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ የአሰራር ሥርዓት መከተል፤
4. በገበያ ተወዳዳሪነትን ማበረታታት፤
5. የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት፤
6. ጥራትና ምርታማነትን ማሻሻል፤

ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ አምራች ኢንዱስትሪዎች ልየታና ምልመላ

6. ስለ ተጠቃሚዎች ልየታና ምልመላ

1. ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ የመስሪያ ቦታ አልሚው እና መሬት አቅራቢ ተቋማት አልምተው በሚያቀርቡት የመስሪያ ቦታ ስታንዳርድ መሰረት የተጠቃሚነት መስፈርት በማዘጋጀት አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመመልመል ለውሳኔ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች አዲስ የመስሪያ ቦታ እና ማስፋፊያ ጥያቄ በጽህፈት ቤቱ ፕሮሰስ ካውንስል አጽድቆ ለቢሮው ይልካል፤
3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጽህፈት ቤቱ ፀድቆ የተላከለትን የአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቢሮው የፋሲሊቴሽንና ካይዘን ዘርፍ አስተባባሪነት ከአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ ጋር በጋራ ተገምግሞ ለቢሮ ስትራቴጂክ ካውንስል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለኤጀንሲው ይልካል፤
4. የመካከለኛ እና የከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚቀርቡ አዲስ የመስሪያ ቦታ፣ ማስፋፊያ እና የመሬት ጥያቄ በፋሲሊቴሽንና ካይዘን ዘርፍ አስተባባሪነት ከአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ ጋር በጋራ በመሆን ይለያል፤ ይመለምላል፤ ይገመግማል፣ ለቢሮው ስትራቴጂክ ካውንስል ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤
5. ከዚህ በፊት በመንግስት መስሪያ ቦታ ላይ ተጠቃሚ ያልነበሩ ነገር ግን ተከራይተው ወይም በግል ይዞታቸው የሚሰሩ ከፍተኛ የመሰሪያ ቦታ ችግር ያለባቸውን አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመስሪያ ቦታ ወይም ኢንዱስትሪ ፓርክ ሊገቡ የሚችሉ ወይም የመሬት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው መመልመያ መስፈርት መሰረት ፍትሃዊነትና ግልፀኝነት ባለው አሰራር በማወዳደር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይችላል፡፡

7. ስለመስፈርት

አዲስ የመስሪያ ቦታ፤ የማስፋፊያ እና መሬት ጥያቄ ያላቸው ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና ክላስተር ማዕከላት ሊገቡ የሚችሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉትን መመልመያ መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማቅረብ፣
2. የሚቀርበው ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ካለው የመስሪያ ቦታ ጋር የሚጣጣም መሆኑ፣
3. የእድገት ደረጃው አነስተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፣
4. ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለው እና የዘመኑን የገቢ ግብር የከፈለ ከሆነ፣
5. የፈጠረውና ወደ ፊት የሚፈጥረው ቋሚ የስራ ዕድል፣
6. ተኪ ምርት የሚያመርት መሆኑ፣
7. ምርት በራሱ በቀጥታ ወደ ውጪ የሚልኩ ወይም ኤክስፖርት የሚያደርግ፣
8. የተሻለ የማምረት አቅም ያለው፣
9. ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለ ስለመሆኑ፡፡

## 8. ስለውድድር

1. በአንቀጽ 7 ከንዑስ አንቀጽ (1) እሰከ (4) የተዘረዘሩት እንደ ቅድመ ሁኔታዎች ይወሰዳሉ፣ ከንዑስ አንቀጽ (5) እስከ (9) የተጠቀሱትን መስፈርቶች መነሻ በማድረግ በዚህ መመሪያ በአባሪነት በተቀመጡት የማወዳደሪያ ነጥቦች መሰረት ተመዝነው ውጤት ይሰጣል፣
2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ውጤት የተሰጣቸውን አምራች ኢንዱስትሪዎች ባመለከቱት ጊዜ እና ባገኙት ውጤት መሰረት ቅደም ተከተል በማስያዝ ዝርዝራቸው ለኤጀንሲው ይላካል
3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ተወዳድረው እኩል ውጤት ካመጡ ተወዳዳሪዎች በፈጠሩት ቋሚ የስራ ዕድል፣ ባስመዘገቡት ተኪ ምርት እና ሽያጭ መጠን፣ በኤክስፖርት ባገኙት የዶላር መጠን እና የማምረት አቅም እና ምጣኔ ደረጃ ተመዝነው የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው በቅድሚያ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
4. ሁሉም ተወዳደሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ ተኪ ምርት የሚያመርቱ እና ኤክስፖርት የሚያደርጉ እስካልሆኑ ድረስ ለተወዳዳሪዎች ውጤት የሚሰጠው ከሁለቱ መስፈርት በአንዱ በተኪ ምርት ወይም በኤክስፖርት መጠን ብቻ ይሆናል፣
5. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤክስፖርትና ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ድጋፍ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ከተወዳዳሪዎች መካከል ቅድሚያ ድጋፍ ለማግኘት ተኪ ምርትና

ኢክስፖርት የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፤

6. ወደ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና እንደአስፈላጊነቱ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በሚኖረው መስሪያ ቦታ እየተወዳደሩ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ የኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ክላስተር ማዕከላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል፤
7. እንደአስፈላጊነቱ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከተማው በሚያዘጋጀው ቦታ እና አሰራር መሰረት ለተመረጡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለማምረቻ የሚሆን መሬት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይችላል፤
8. አንድ አምራች ኢንዱስትሪ የሚጠይቀው የማስፋፊያ ቦታ ጥያቄ ወይም አዲስ መስሪያ ቦታ ጥያቄ ወይም በዘርፉ ውስጥ ተሰማርቶ ያለ የማምረቻ ግንባታ የመሬት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በመስፈርቱ መሰረት ተመዝኖ ቢያንስ 70% እና ከዚያ በላይ ነጥብ ሲያገኝ ነው፡

## ክፍል ሶስት

## የካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ፣ የብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ

9. ስለ ካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ፣ የብድር አቅርቦት ተጠቃሚ ልየታና ምልመላ

   1. ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ የካፒታል እቃ እና ሊዝ ፋይናንስ ወይም የብድር ፍላጎት ያላቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች የካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ አቅራቢ ወይም አበዳሪ ተቋማት ባዘጋጁት ወይም በሚያዘጋጁት መመሪያ ወይም አሰራር መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያመቻቻል፤

   2. አምራች ኢንዱስትሪዎች በቀጥታ በየተቋማቶቹ መስፈርት መሰረት የካፒታል ፋይናንስ ወይም ብድር በራሳቸው የማግኘት መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የካፒታል እቃ ወይም የሊዝ ፋይናንስ ወይም ብድር አቅርቦት ፍላጎት ያላቸውን አነስተኛ እና መካከለኛ አምራቾች ጽህፈት ቤቱ እንደየስራው አደረጃጀት በአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ዘርፍ አስተባባሪነት ወይም የፋሲሊቴሽን ካይዘን ዘርፍ አስተባባሪነት በጋራ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጽህፈት ቤቱ ፕሮሰስ ካውንስል ፀድቆ ለቢሮው ይልካል፤
   3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ

የካፒታል እቃ ወይም የሊዝ ፋይናንስ ተጠቀሚ እንዲሆኑ የተለዩ የአነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጽህፈት ቤቱ ፕሮሰስ ካውንስል ፀድቅ ለካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ይላካል፤

4. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚመለከታቸው የፋይናንስ ተቋማት፣ የካፒታል እቃ ወይም የሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በጽህፈት ቤቱ መረጃ ተደራጅቶ ለቢሮው ሲላክ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስተባባሪነት ከፋሲሊቴሽን እና ካይዘን ዘርፍ ጋር በጋራ ታይቶ ለቢሮው ስትራቴጅክ ካውንስል ይቀርባል፤ ከፀደቀ በኋላ ለሚመለከታቸው ለካፒታል እቃ እና ለሊዝ ፋይናንስ ወይም ለፋይናንስ ተቋማት ይላካል፤
5. የካፒታል እቃ ወይም የሊዝ ፋይናንስ ወይም ብድር ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት ያላቸው ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደ አግባብነቱ በቢሮ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስተባባሪነት ወይም በፋሲሊቴሽን እና ካይዘን ትግበራ ዘርፍ አስተባባሪነት በጋራ በመሆን የፍላጎት ጥያቄውን በጥናትና መረጃ አስደግፎ ለቢሮ ስትራቴጂክ ካውንስል ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ለካፒታል እቃ ወይም ለሊዝ ፋይናንስ ወይም ለብድር አቅራቢ ተቋም ይልካል፤ ይከታተላል፤
6. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው አስተዳደር የተደራጁ ወይም በግላቸው በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የካፒታል እቃ ወይም የሊዝ ፋይናንስ ድጋፍ ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ ከካፒታል ዕቃ እና የሊዝ ፋይናንስ ወይም ለአበዳሪ ተቋማት ጥያቄያቸውን በቀጥታ በማቅረብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## 10.<u>ስለመስፈርት</u>

1. የካፒታል እቃ እና የሊዝ ፋይናንስ ወይም የብድር ድጋፍ ጥያቄ አቅራቢ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉትን መመልመያ ወይም መለያ መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

   ሀ) የማፋክቸሪንግ አምራች ኢንዱስትሪ መሆን ፤

   ለ) የሚሰራበት የመስሪያ ቦታ ያለው፤

   ሐ) የእድገት ደረጃው አነስተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፤

   መ) የፈጠረው የስራ እድል፤

ሥ) ተኪ ምርት ወይም ኤክስፖርት ላይ የተሰማራ መሆን ይኖርበታል፤

ረ) የተሻለ የማምረት አቅም እና ምጣኔ፤

ሰ) ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለ፤

ሸ) የዘመኑን የገቢ ግብር የከፈለ ከሆነ፤

2. የካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛ፣ መካከለኛ ወደ ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በካፒታል እቃ ወይም ሊዝ ፋይናንስ ወይም ብድር አቅራቢ ተቋማት፣ በቢሮ ባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የድርድርና ኮሚሽኒንግ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## ክፍል አራት

## የገበያ ትስስርና ፕሮሞሽን

### 11. ስለ ገበያ ትስስር

1. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ፣ በክልል እና በውጪ ሀገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
2. በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ተቋማት የሚገኙ የገበያ መረጃዎች በማሰባሰብና አጋርነት በመፍጠር የገበያ ትስስር ይደረጋል፤
3. አምራች ኢንዱስትሪዎች እርስ በእርሳቸው በምርትና ግብዓት እንዲተሳሰሩ በማድረግ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
4. በቅዳሜና እሁድ፤ በንግድ ትርኢትና ባዛር፤ በሸማች ማህበራት ሱቅ እና በምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከላት ምርትና አገልግሎት በመሸጥ የገበያ ትስስር ይፈጠራል፤
5. ከከተማው የንግድና ዘርፍ ማህበራት ጋር በመቀናጀት በስሩ ካሉት የንግድ ድርጅቶች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ጋር አምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር እንዲፈጥሩ ይደረጋል፤
6. በሀገር እና ከሀገር ውጭ የገበያ መዳረሻዎችን በጥናት በመለየት አምራች ኢንዱስትሪዎች በማስተሳሰር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
7. በከተማ አስተዳደሩ የግዢ መመሪያ መሰረት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ወይም ኢንተርፕራይዞች በተሰጣቸው ወይም በሚሰጣቸው ልዩ አስተያየት የገበያ ትስስር ተፈፃሚ ይሆናል፤
8. አምራች ኢንዱስትሪዎች በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ ድጋፍ ይደረጋል፤

9. አምራች ኢንዱስትሪዎች የምርት ጥራትና ስታንዳርድ፣ የምርት ግብዓት መግለጫ፣ የአስተሻሸግ እና የክህሎት ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ ድጋፍ ይደረጋል፤
10. አምራች ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን የንግድ ስም እና መለያ እንዲኖራቸው በማድረግ ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

12. <u>በመንግስት ተቋማት የሚፈጠር የገበያ ትስስር ምልመላ</u>

1. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ምልመላ መከናወን አለበት፤
2. ገበያውን ከፈጠረው ተቋም የሚዘጋጁ መስፈርቶች ከዕድገት ደረጃ ጋር የማይገናዘቡ ሆኖ ሲገኝ ገበያውን ከሚፈጥረው ተቋም ጋር በመወያየትና መስፈርት በማዘጋጀት ምልመላ የሚከናወን ይሆናል፤
3. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም መስፈርት ሳያዘጋጅ ስራውን ለማሰራት ጥያቄ ካቀረበ በቢሮው የአሰራር ማዋል መሰረት ስራው ከሚጠይቀው የሰው ኃይልና ካፒታል አንፃር መስፈርት በማዘጋጀት ምልመላ የሚከናወን ይሆናል፤
4. በዚሁ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የምልመላ ሂደትን የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም ጥያቄ ሲያቀርብ በቢሮው የካይዘንና ፋሲሊቴ ዘርፍ ባሉ ዳይሬክቶሬቶች ስታንዳርድና መመልመያ ማኑዋል አዘጋጅቶ በፐሮሰስ ካውንስል ተገምግሞ በቢሮው ስትራቴጅክ ካውንስል ማኑዋሉ ጸድቆ ተግባራዊ ይደረጋል፤
5. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጸደቀው ማኑዋል መሰረት ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መንገድ እና በገበያ ትስስሩ የገንዘብ መጠን ልክ ወረፋ በማስያዝ በቅደም ተከተላቸው ትስስሩ የሚከናወን ይሆናል፤
6. ከሀገር ውስጥም ይሁን ከውጭ የገበያ ትስስር የሚፈጠርለት አምራች ኢንዱስትሪ በሚመለከት ለተጠየቀው የግብይት መጠን በቂ ምርት ማምረት እና በወቅቱ ማምረት እና ማቅረብ ይጠበቅበታል፤
7. ለአንድ አምራች ኢንዱስትሪ ከአንድ ጊዜ በላይ ትስስር ሊፈጠር የሚችለው በተመሳሳይ ዘርፍ ውስጥ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሌሉ እና በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት በድጋሜ ተራው ሲደርሰው ብቻ ይሆናል፤
8. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የትስስሩ ተጠቃሚ

ያልሆኑ ቅድሚያ የማግኘት እና የትስስሩ የገንዘብ መጠንን በማየት ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መንገድ ትስስር የሚፈጠር ይሆናል፤

9. በዚሁ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (8) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የገበያ ትስስር ድጋፍ ጥያቄ አቅራቢ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉትን መመልመያ ወይም መለያ መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-
    ሀ) ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፣
    ለ) ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርብ፣
    ሐ) የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል በሮል የሚያቀርብ፣
    መ) የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት፣
    ሠ) ማህበራዊ ተሳትፎ፣
    ሰ) የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት ያስለካ፤
10. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ በአባሪ 2 የተገለጹት ዝርዝር የአምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር ድጋፍ ፍላጎት መመልመያ መስፈርት መሰረት ተግራዊ ይደረጋል፡፡

13. <u>ስለ ገበያ መረጃ</u>

1. በተለያዩ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች የሚወጡ የጨረታ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፤
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ እና ከግል ተቋማት ጋር በመቀናጀት የጨረታ መረጃ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

14. <u>የገበያ ትስስር መጠን በብር</u>

1. የሚፈጠር የገበያ ትስስር የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፡-
    ሀ) ለአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪ ከ600,001 (ከስድስት መቶ አንድ) እስከ 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) የገበያ ትስስር ይፈጠራል፤
    ለ) ለመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ ከ10,000,001 (ከአስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) የገበያ ትስስር ይፈጠራል፤
    ሐ) ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ ከ90,000,001 (ከዘጠና ሚሊዮን አንድ) በላይ የገበያ ትስስር ይፈጠራል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ተራ ፊደል (ሀ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የአሰሪው መስሪያ ቤት የፈጠረውን የገበያ ትስስር ወቅታዊ መረጃ በመሰብሰብ መያዝ አለበት፤
3. የገበያ ዕድል ያገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተገቢውን ሌሎች የእድገት ደረጃ ድጋፍ እየተሰጣቸው የገበያ ትስስር ጣሪያ ሲደርሱ ክትትል እየተደረገ ወደ ቀጣዩ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፤
4. አንድ ጊዜ የገበያ ትስስር ያገኘ አምራች ኢንዱስትሪ ሁለተኛ ጊዜ ትስስር የሚደረግለት በዘርፉ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሌሎች አምራች ኢንዱስትሪዎች የመጀመሪያ ትስስር ማግኘታቸውን በማረጋገጥ መሆን አለበት፤
5. የገበያ ትስስር የሚደረግለት አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃና ንግድ ፍቃድ ያሳደሰ መሆን አለበት፡፡

15. <u>ስለ ግብይት ስልቶች</u>

በሚከተሎት የግብይት ስልቶች መሰረት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡-

1. በንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ስልት አምራች ኢንዱስትሪዎች ስራውን ከወሰደው አካል ጋር ውል በመግባት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
2. በአውት ሶርሲንግ የግብይት ስልት በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት አውትሶርስ ሊደረጉ የሚገባቸውን ሥራዎች በጥናት በመለየት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
3. በፍራንቻይዚንግ የግብይት ስልት አምራች ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥና በውጪ ከሚገኙ ድርጅቶች የንግድ ምልክታቸውን፤ የንግድ ፈቃዳቸውን፣ የምርት ስታንዳርዳቸውን በመጠቀም ምርቶችን እንዲያመርቱና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ፤ እንዲያከፋፍሉ ወይም በኮሚሽን ለመሸጥ እንዲችሉ እንደ የእድገት ደረጃቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤
4. በአውትግሮወር የግብይት ስልት የግብርና ውጤቶችን በማዘጋጀትና እሴት በመጨመር ስራውን ለሰጠው አካል እንዲያቀርቡ በማድረግ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

16. <u>የገበያ ትስስር የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>

1. የተሰጠውን ስራ በገባው ውል መሰረት መፈጸም ሳይችል ሲቀር፤
2. የተጭበረበረ መረጃ አቅርቦ ሲገኝ፤

3. በዕድገት ደረጃው የተቀመጠለትን የገበያ ትስስር ጣሪያ ሲያልፍ፤
4. ህጋዊ ሰውነት በህግ አግባብ ሲታገድና ሲፈርስ፤
5. የእድገት ደረጃ ሽግግር ሰርትፊኬት ያላገኘ ወይም ያላሳደሰ ከሆነ፤
6. ሌሎች አሳማኝና አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፡፡

17. <u>ምርትና አገልግሎት ስለማስተዋወቅ እና ሽያጭ</u>

የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት በኤግዚቢሽንና ባዛር፣ በድረ-ገጽ፣ በየንዑስ ዘርፍ በሚዘጋጅ የምርት ካታሎግ ፣ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች ፣ በምርት ማሳያና መሸጫ ሱቅ እና ቦታዎች ፣ በመጽሔት ፣ በብሮሸር፣ በበራሪ ወረቀት ፣ ቢዝነስ ካርድ ፣ በቴሌቪዥንና ሬዲዮ ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ፣ በቢል-ቦርድ ፣ የቅዳሜና እሁድ ቀን ገበያ እና በሌሎች የማስተዋወቂያ ዘዴዎች እንዲሸጡና እንዲያስተዋውቁ ይደረጋል፡፡

18. <u>በኤግዚቢሽንና ባዛር ምርትና አገልግሎትን ስለማስተዋወቅ</u>

1. በኤግዚቢሽንና ባዛር ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች የፈጠራ ስራ ያላቸው ፣ ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር የሚልኩ ፣ የውጪ ምርት የሚተኩ እና ተሞክሮ ያላቸው እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
2. በኤግዚቢሽንና ባዛር ዝግጅት አምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉም ሆነ በከፊል ወጪ በመጋራት ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ ይደረጋል፤
3. የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎት ለማስተዋወቅና ለመሸጥ የሚያስችል ቋሚ የኤግዚብሽን ወይም የባዛርና አውደ ራዕይ ወይም ኢምፓሪየም ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤
4. በተናጥል ኤግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት የማይቻል ከሆነ ከሌሎች አጋር እና በስራው ከተሰማሩ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤
5. በክልሎች፣ ከተማ አሰተዳደሮች እና በውጭ ሀገር በሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር ከሚያዘጋጁ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
6. በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚቀርቡ ምርት በሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የተመረቱ እና በውጭ ሀገር ባለሀብት የተመረተ ምርት ከሆኔ በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ከሚመለከተው አካል የሽያጭ ፍቃድ ያለው መሆን አለባቸው፤

7. በኢምፖሪየም እና ኤክስፖ ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅና ለመሸጥን እንዲያስችል የመመልመያ መስፈርት በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ይደረጋል፤ በየደረጃው በሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር የአምራች ኢንዱስትሪ ምልመላና ተያያዥ ስራዎች ድጋፍ ከሚሰጡ የስራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት ይተገበራል፡፡

19. <u>የኤግዚቢሽንና ባዛር የምልመላ መስፈርት</u>

1. የታደሰ ዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ያለው፤
2. ከንግድ ዘርፍ ውጪ ያለ አምራች ኢንዱስትሪ የራሱን ምርት ብቻ የሚያቀርብ፡፡

20. <u>ስለ ኤግዚቢሽንና ባዛር ተሳትፎ</u>

1. ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ፤
2. ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
3. የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
4. የማሽነሪና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
5. የእንጨትና ቀርከሃ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
6. የምግብ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
7. የመጠጥ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
8. የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
9. የዕደ ጥበብ ዉጤቶችና ጌጣጌጥ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
10. የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
11. የወረቀት ምርትና ህትመት ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
12. የግንባታ ግብዓት ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
13. ብረት ያልሆኑ የማዕድን ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
14. የኮምፒወተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የእይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤
15. መሰረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ፤

16. በዚሁ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (15) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ኤግዚቢሽንና ባዛሩ ዓላማ የንዑስ ዘርፍ የተሳትፎ መጠን ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል፤
17. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (16) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ስር የሚገኙ ንዑስ ዘርፎችንም የሚያካትቱ ይሆናል፡፡

21. <u>ከክፍለ ከተማ ውጪ የሚደረግ የኤግዚቢሽንና ባዛር ተሳትፎ መሟላት የሚገባቸው</u>

**መስፈርቶች**

1. አዘጋጁ ክፍለ ከተማ፤ በክፍለ ከተማው ውስጥ ለሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት ተጨማሪ ቦታ ካለው ብቻ ከሌላ ክፍለ ከተማ ማሳተፍ ይችላሉ፤
2. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ ወይም የፈጠራ ስራ ያላቸው ወይም ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠሩ ወይም ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር የሚልኩ ወይም የውጪ ምርት የሚተኩ መሆን አለባቸው፡፡

22.**በኢግዚቢሽንና ባዛር ወቅት የሚደረግ ክልከላ**

1. የውጭ ሀገር ምርቶችን ይዞ መገኘት፤
2. አምራች ኢንዱስትሪው ከራሱ ምርት ውጪ ይዞ ከገባ ወይም ከተገኘ፤
3. የኢግዚቢሽንና ባዛር ቦታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ፤
4. ሰላማዊ እንቅስቃሴ ማወክ፤
5. መረጃ ለሚመለከተው አካል መከልከል፤
6. ሳይፈቀድለት ተሳታፊ ሆኖ ከተገኘ፤
7. ያልተፈቀደና የተከለከለ ምርት ይዞ መገኘት፡፡

23.**ኢግዚቢሽንና ባዛር ክልከላን በሚተላለፍ ላይ የሚወሰድ እርምጃ**

1. ለመጀመሪያ ጊዜ ክልከላውን የተላለፈ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤
2. ለሁለተኛ ጊዜ ክልከላውን የተላለፈ ለአንድ ዓመት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤
3. ለሶስተኛ ጊዜ ክልከላውን የተላለፈ በኤግዚቢሽንና ባዛር እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡

24.**ስለ ጥሬ እቃ ግብዓት**

1. የጥሬ ዕቃ ፍላጎት በዝርዝር በዓይነት ፤ በዋጋ ፤ በጥሬ ዕቃው መገኛ ቦታ እና በመጓጓዣ ወጪ ተለይቶ ከጥሬ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ትስስር ይፈጠራል፤
2. የጥሬ ዕቃ አቅራቢ የአምራች ኢንዱስትሪዎች በክላስተር ማዕከላት ጥሬ ዕቃ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፤
3. በጥሬ እቃ አቅርቦት የሚተገበሩ ስራዎች ከድጋፍ ሰጪ የስራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

25.**የድጋፍና እና ክትትል ስራዎች**

በመመሪያ የተቀመጡ አሰራሮችን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍና ክትትል ማኑዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የካይዘን ትግበራ ማረጋገጥ

### 26.ስለ ካይዘን ቅድመ ትግበራ

1. ቢሮው ለከተማ አስተዳደሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የካይዘን አገልግሎት በመስጠት ጥራትና ምርታማነታቸው እንዲሻሻል ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፤
2. ካይዘንን ለሚተገብሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ የመመልመያና መመዘኛ መስፈርቶች በማውጣት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት አገልግሎቱን ማግኘት የሚኖርባቸው አምራች ኢንዱስትሪዎችን ትግበራውን ለማካሄድ የሚያስችል ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በመመካከር የሚያስፈልጋቸውን ጊዜያዊ አደረጃጀት እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡

### 27.ስለ አምራች ኢንዱስትሪዎች አመራር

1. ትግበራ በሚካሄድባቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈጠሩ አደረጃጀቶች በአምራች ኢንዱስትሪው የበላይ ኃላፊ የሚመሩ ሆነው የሚከተሉትን አካላት በዋናነት የሚይዝ ይሆናል፡-
   ሀ) በአምራች ኢንዱስትሪው የበላይ ኃላፊ የሚመራ አብይ የካይዘን ልማት ቡድን፣
   ለ) ትግበራ የሚካሄድባቸው የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ዳይሬክተሮች፣ ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርግ የተቋሙ አመቻች ባለሙያ ወይም ኃላፊ፤
   ሐ) ትግበራ በሚካሄድባቸው የሥራ ክፍሎች በባለሙያዎች የሚደራጅ የልማት ቡድን ይይዛል፤
2. ቢሮው ትግበራውን የሚደግፍ የካይዘን አማካሪ ሊመድብ ይችላል፡፡

### 28.ካይዘን ተግባራዊ ከሚደረግባቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚጠበቁ ተግባራትና ኃላፊነቶች

1. ከይዘን ተግባሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተዘጋጅቶ በሚቀርበው

የትግበራ እቅድ መሠረት ለሥራው የሚያስፈልግ ተመጣጣኝ የሆነ በጀት ይመድባል፤

2. አምራች ኢንዱስትሪው የበላይ አመራር ሥራውን የሚመራበት፣ የሚከታተልበትና የሚገመግምበት የማስተግበሪያ ተቋማዊ እቅድ ከቢሮው ጋር በመነጋገር ያቅዳል፤ ይመራል፤
3. አምራች ኢንዱስትሪው አጠቃላይ አመራርና ሠራተኞች በተገኙበት የትግበራ እቅድ እወጃ እና ከቢሮ ጋር የትግበራ ስምምነት ሰነድ ይኖረዋል፤
4. በትግበራ ምዕራፍ ወቅት አመራሩ የፕሮግራሙን ውጤታማነት፣ የመከታተል፣ የመደገፍና የመጣውን ለውጥ የማስተዋወቅ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

29.<u>በካይዘን ትግበራ ከቢሮው የሚጠበቁ ተግባራትና ኃፊነቶች</u>

1. ቢሮው ትግበራ በሚካሄድባቸው የከተማ አስተዳደሩ አምራች ኢንዱስትሪ የካይዘን ትግበራ አፈጻጸምን የመከታተል፣ የመደገፍ እና ብቁ የካይዘን አማካሪ የመመደብ ኃላፊነት አለበት፤
2. ቢሮው በካይዘን ሥልጠናና ትግበራ ሂደት የሚገኝ ምርጥ የትግበራ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. ቢሮው በካይዘን አተገባበር የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና አካላት በሚዘረጋው የእውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት መሠረት እውቅና ይሰጣል፡፡

30.<u>ስለ ካይዘን ትግበራ ጥራት ማረጋገጥ</u>

1. በመጀመሪያ ደረጃ ካይዘን ትግበራ የ5ቱ "ማ" እና ሌሎች የካይዘን ትግበራ ሂደት ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ወሰኖች /Scope/ ስልጠና፣ እቅድ፣ ማጣራት፣ ማስቀመጥ፣ ማጽዳት፣ ማላመድ፣ ማዝለቅ፣ ደህንነት እና ከይዘን ልማት ቡድን አሠራርና አተገባበር የሚታዩ የተለያዩ ዝርዝር ጉዳዮች በምን ያህል አግባብነት ወይም ደረጃ ተተግብረው እንደሆነ ይረጋገጣል፤

2. አምራች ኢንዱስትሪዎች ከይዘንን መተግበራቸው በ5ቱ "ማ" የፍተሻና መመዘኛ መርህ መሰረት እና ሌሎች የካይዘን ማስተግበሪያ ቴክኒኮች ተግባራዊነቱ እና ቀጣይነቱን 75% እና በላይ መተግበሩ ይረጋገጣል፣
3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ በአባሪ 3 የተገለጹት ዝርዝር የአምራች ኢንዱስትሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ካይዘን ትግበራ የፍተሻ እና መመዘኛ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ ይደረጋል፣
4. በየደረጃው የሚካሄድ ትግበራዎች እንደ አምራች ኢንዱስትሪው ነባራዊ ሁኔታ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ቆይታ ይኖረዋል፣
5. የካይዘን ስልጠና እና ትግበራ ከተጀመረና ወጪ ከወጣ በኋላ አምራች ኢንዱስትሪው በቸልተኝነት ወይም በአለመተባበር ዳር ሳይደርስ ትግበራውን ማቋረጥ አምራች ኢንዱስትሪው ከሚያገኛቸው ሌሎች መንግስታዊ ድጋፎች ውጭ የሚሆን ይሆናል፣
6. የካይዘን ትግበራ እና ማረጋገጥ ተግባርን ለመፈጸም የሚያስችሉ የድጋፍና ክትትል ማስተግበሪያ ማኑዋል መሰረት በማድረግ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡
7. የካይዘን ትግበራ ሂደቱን ጠብቆ ብቁ ለሆኑ እና ትግበራውን ለአዘለቁ አምራች ኢንዱስትሪዎች የዕውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀት</u>

### 31.<u>የዘርፍ ማህበራት አደረጃጀት</u>

1. አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደ ስራ ባህሪያቸው እና እንደተሰማሩበት ዘርፍ ወይም ንዑስ ዘርፍ መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ በማህበር ይደራጃሉ፣
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በክፍለ ከተማ እና በከተማ ደረጃ እንዲደራጅ ይደረጋል፣
3. የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ሲመረጥ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሆኖ ንዑስ ዘርፉን መሰረት በማድረግ አባላት መመረጥ አለበት፣
4. በክፍለ ከተማ ደረጃ የዘርፍ ማህበራት በጋራ በመሆን በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት የክፍለ ከተማ የዘርፍ ማህበራት እንዲመሰርቱ ይደረጋል፣

5. በከተማ ደረጃ የዘርፍ ማህበራትን ለማደራጀት በየክፍለ ከተማው የተቋቋሙ የዘርፍ ማህበራት በጋራ በመሆን በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት የከተማ የዘርፍ ማህበራት እንዲመሰርቱ ይደረጋል፤
6. በየደረጃው የሚደራጁ የዘርፍ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ግዴታቸውን በመወጣት ጥቅሞቻቸውን በማስጠበቅና የሚገጥማቸውን ችግር በጋራ ይፈታሉ፤
7. በየደረጃው የሚመረጥ የዘርፍ ማህበራት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲመረጥ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣ ከወንጀል ድርጊቶች ነጻ የሆነ ፣ የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያለው፤ በስራው ውጤታማ የሆነ፤ ስራዎችን አቅዶ የመስራት አቅም ያለው፤ የማስተባበር ችሎታው ያለው፤ ከሌሎች ጋር በጋራ የመስራት ፍላጎት ያለውና በአመራርነት ለማገልገል ፍቃደኛ መሆን አለበት፤
8. የዘርፍ ማህበራት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሶስት ዓመት የቆይታ ጊዜ የሚኖራቸው ሲሆን አባላቱ ካመኑበት ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል፤
9. የአገልግሎት ዘመናቸውን ሳይጨርሱ በተለያየ ምክንያት የሚጓደሉ አመራሮች በሚኖሩበት ወቅት የምክር ቤቱን ጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ በመጥራት በጎደሉት አባላት የመተካት ስራ መስራት አለበት፡፡

## 32.<u>የዘርፍ ማህበራት ስለሚደራጁበት ንዑስ ዘርፎች</u>

በከተማ ሆነ በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማህበራት በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ በሚካተቱ ንዑስ ዘርፎች ተሰማርተው የሚገኙና ወደ ፊት በንዑስ ዘርፍ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ማናቸውም ተቋማት እንደየ ንዑስ ዘርፋቸው ተመጋጋቢነት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በዘርፍ ማህበራት መደራጀት ይችላሉ፡፡

## 33.<u>የዘርፍ ማህበራት በየደረጃው ካለው የተቋሙ አደረጃጀት ጋር የሚኖረው ግንኙነት</u>

1. የዘርፍ ማህበራት በየደረጃው ካሉ የተቋሙ አመራሮች ጋር ተቀራርቦ ይሰራል፤
2. በተቋሙ እቅድ ውይይት እና የእቅድ አፈፃፀም ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፤
3. አጠቃላይ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራሉ፡፡

## 34.<u>ስለዘርፍ ማህበራት ምዝገባ ሰርተፍኬት አሰጣጥ</u>

1. በክፍለ ከተማ የሚደራጅ የዘርፍ ማህበር የሁሉንም አባላት ስምና ፊርማ ያለበት የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ በክፍለ ከተማ የኢንዱስትሪ

ልማት ጽህፈት ቤት ታይቶ ሰርትፍኬት በሚመለከተው እንዲሰጥ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

2. በከተማ የሚደራጅ የዘርፍ ማህበር ከየክፍለ ከተማው የሚወከሉ አመራሮችን ዝርዝር የያዘ በክፍለ ከተማ የኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የተፃፈ የእውቅና ደብዳቤ እና መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ በከተማ የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ታይቶ የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም የከተማ ዘርፍ ማህበር ሰርተፍኬት ይሰጣል፡፡

## 35.<u>የመተዳደሪያ ደንብ ይዘት</u>

በየደረጃው የሚቀርብ የመተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚይዝ ይሆናል፡-

1. የዘርፍ ማህበሩ ስም፣
2. የዘርፍ ማህበሩ አድራሻ፣
3. የዘርፍ ማህበሩ አላማ፣
4. የዘርፍ ማህበሩ የተመሰረተበት ቀን፣
5. የዘርፍ ማህበሩ አርማ፣
6. የዘርፍ ማህበሩ መሪዎች መመዘኛ፣
7. ስለ ዘርፍ ማህበሩ አባላት መዋጮ፣
8. ስለ ዘርፍ ማህበሩ ንብረትና ገንዘብ አያያዝ፣
9. ስለ ዘርፍ ማህበሩ ስብሰባዎችና ምርጫ አፈፃፀም፣
10. ስለ ዘርፍ ማህበሩ አባላት መብትና ግዴታ፣
11. ስለ ዘርፍ ማህበሩ ስነሥርዓት እርምጃዎች አወሳሰድ፣
12. ዘርፍ ማህሩ ስለሚፈርስበት ሁኔታ፣
13. ዘርፍ ማህበሩ በሚፈርስበት ጊዜ ስለ ንብረት አወሳሰን ጉዳይ የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 36.<u>የድጋፍ እና ክትትል ስራን በተመለከተ</u>

በዚህ መመሪያ ስለዘርፍ ማህበራት የተደነገጉ አሰራሮችን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍና ክትትል ማኑዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 37.<u>የአምራች ኢንዱስትሪ  ልማት ምክር ቤት</u>

1. የሚቋቋመው የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ምክር ቤት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተቀመጠው አሰራር መሰረት በከተማ እና በክፍለ ከተማ ደረጃ ስራዎችን አቀናጅቶ ለመምራትና የአምራች ኢንዱስትሪ ስራዎች የአመራር ትኩረት እንዲያገኙ የሚቋቋም እና በተዋቀረው አደረጃጀት መሰረት የሚደራጅ ይሆናል፤

2. የምክር ቤት አደረጃጀቱም እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፤
3. በየዓመቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫና የአሰራር መመሪያና የአፈፃፀም ማኑዋል መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር

### 38.ስለ የዕድገት ደረጃ አወሳሰን

1. አምራች ኢንዱስትሪው የያዘውን የሰው ኃይልና የካፒታል መጠን መሰረት በማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስራ ሲገባ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ወይም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ መሰጠት ይኖርበታል ፤
2. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ወይም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ለማግኘት የሰው ሃይል ብዛትና የካፒታል መጠን የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ በካፒታል መጠን የሚወሰን ይሆናል፤
3. በተለያዩ ምክንያቶች ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ ሊሸጋገሩ ያልቻሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የካፒታል እና የሰው ኃይላቸውን መሰረት በማድረግ እና ቢሮው በመመዘን ደረጃ ይሰጣል፤
4. ከዚህ በፊት የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ያልተሰራላቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች በመስፈርቱ መሰረት ተመዝነው በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ተፈርጀው ሰርተፊኬት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### 39.የነባር አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሽግግር

1. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ መስፈርቱን እስካሟላ ድረስ በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ወይም ወር እና ቀን የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሊያደርግ ይችላል፤
3. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሽግግር መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ ወደ የትኛውም የዕድገት ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል፤
4. የደረጃ ዕድገት ሽግግር ሲሰጥ እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደስራ ባህሪው ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቀሙ እና አነስተኛ የሰው ኃይል የሚፈልጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ካፒታላቸው እንደ ቅድሚያ መስፈርት ተወስዶ ሊታይላቸው

ይችላል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው መረጃው ተደራጅቶ ለዘርፍ ኃላፊ ሲቀርብ እና በዘርፍ ፕሮሰስ ካውንስል ታይቶ በቢሮ ስትራቴጂ ካውንስል ሲጸድቅ ነው፤
6. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ በዕድገት ደረጃ መስፈርት ተመዝኖ ከመቶ ያገኘው ውጤት ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ ሊያሸጋግረው የሚችል ቢሆንም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመጣው ደንብ ቁጥር 526/2015 ትርጉም ላይ የተመላከተውን የዕድገት ደረጃ ሽግግር የሀብት መጠን ካላሟላ ወደ ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገር አይችልም፤
7. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ በሶስት ዓመት ውስጥ ከነበረበት የዕድገት ደረጃ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር ይኖርበታል፤
8. የቢሮ እና የጽህፈት ቤቶች የሥራ ድርሻ፦
   ሀ) የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤቶች የአምራች ኢንዱስትሪዎቹን መረጃ በማደራጀት በጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ጸድቆ ለቢሮ ይልካሉ፤
   ለ) ቢሮው ከክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤቶች የተላከውን መረጃ በማደራጀት እና መስፈርቱን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ በፋሲሊቴሽን እና ካይዘን ትግበራ ዘርፍ ፕሮሰስ ካውንስል ታይቶ በቢሮው ስትራቴጅክ ካውንስል እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

## 40. <u>የነባር አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት እድሳት</u>

1. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት ማሳደስ የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት የቆይታ ጊዜውን ጨርሶ በሁለት ወር ውስጥ ካላሳደሰ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤
3. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሰረት በአንድ ወር ውስጥ ካላሳደሰ የዕድገት ደረጃው ሠርተፍኬት ተሰርዞ ከድጋፍ ማዕቀፍ ውጪ ይሆናል፤
4. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ ቀደም ብሎ በያዘው የእድገት ደረጃ ላይ ያለ ወይም ዝቅ ያለ ከሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት ዕድሳት

ተደርጎለት ለሚመለከተው የስራ ክፍል በፅሁፍ በማሳወቅ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኝ ክትትል ይደረጋል፤

5. በተሰጠው ተጨማሪ ድጋፍ መሰረት ድጋፉን ከሰጠው የስራ ክፍል መረጃ በመሰብሰብና በማረጋገጥ ለውጥ ካላመጣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የዕድገት ደረጃ ሠርተፊኬቱ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲታደስ ይደረጋል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አምራች ኢንዱስትሪ ለሶስተኛ ጊዜ ለውጥ ካላመጣ የዕድገት ደረጃ ሠርተፊኬቱ ተሰርዞ የድጋፍ ማዕቀፍ ተጠቃሚ አይሆንም፤
7. አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ እድገት ሰርቲፊኬት እድሳት ለማድረግ ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፡-
   ሀ) ህጋዊ ንግድ ምዝገባና ፈቃድ ያለው፣
   ለ) የኦዲት ወይም የሒሳብ ሪፖርት ማቅረብ የሚችል፣
   ሐ) የፈጠረውን ቋሚ የሥራ እድል በፔሮል ማቅረብ የሚችል፣
   መ) የዘመኑን ግብር ስለመክፈሉ የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርብ፣
   ሠ) የባለቤቱ ወይም የሥራ አስኪያጁ ህጋዊ የታደሰ የመኖሪያ መታወቂያ ማቅረብ የሚችል፣
   ረ) ዘመናዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ የዘረጋ መሆኑን ከክፍለ ከተማ ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ማቅረብ የሚችል፣
   ሰ) በየደረጃው ያለው ኢንዱስትሪ ልማት ተቋም የሚጠይቀውን ህጋዊ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ የሆነ፣
   ሸ) ካይዘን ለመተግበር ዝግጁ የሆነ፤
8. የደረጃ ዕድገት ሠርተፍኬት ዕድሳት አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ፡-
   ሀ) አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪ በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚታደስላቸው ይሆናል፣
   ለ) መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቢሮ የሚታደስላቸው ይሆናል፣
   ሐ) እያንዳንዱ ሰርተፊኬት ሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ አንዱ ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ቀሪ ሆኖ በፋይሉ ይያያዛል፣
   መ) በክፍለ ከተማ የእድሳት ሰርተፊኬቱ የሚጸድቀው በጽህፈት ቤት ኃላፊ ፊርማ ይሆናል፤ በከተማ ደረጃ በቢሮ በዘርፍ ኃላፊ ወይም የዘርፍ ኃላፊው

በሚወክለው መሰረት የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

41.<u>የዕድገት ደረጃ ሠርተፍኬት ስለሚሰጥባቸው ዘርፎች</u>

1. የዕድገት ደረጃ የሚሰጣቸዉ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ያወጡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ይሆናል፤
2. በህብረት ስራ ማህበር ወይም በየትኛውም ዘርፍ ንግድ ምዝገባና ፍቃድ ያላወጣ የዕድገት ደረጃ የማይሰጠው ይሆናል፡፡

42.<u>የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃዎች</u>

አምራች ኢንዱስትሪዎች የያዙትን የሰው ኃይልና የሀብት መጠን መሰረት በማድረግ በሶስት ደረጃዎች በአነስተኛ ፣ በመካከለኛ እና በክፍተኛ እንዲያልፉ የሚደረግ ሲሆን የሚሰጣቸው የድጋፍ ዓይነትም ያላቸውን የዕድገት ደረጃ ያገናዘበ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለማደግ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች</u>

43.<u>በሥራ እድል ፈጠራ በሃብት፣ በገበያ፣ በትርፋማትና በምርታማነት መጠን</u>

1. የአምራች ኢንዱስትሪው ባለቤትን፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ51 እስከ 100 ሰዎች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን አለበት፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያንቀሳቅሱት የሀብት መጠን ከብር 10,000,001 እስከ 90,000,000 መሆን አለበት፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሃብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሃብት ገዢ መስፈርት ይሆናል፤
4. ከጠቅላላ ሃብቱ ውስጥ 40% እና በላይ ለቋሚ ንብረት ያዋለው መሆን አለበት፤
5. ዓመታዊ የግብይት ሽያጭ መጠን ከብር 10,000,001 እስከ 90,000,000 መሆን አለበት፤
6. ምርትና አገለልግሎቱን ለማስተዋወቅ ቢያንስ አራት (ኢ- ኮሜርስ፣ በብሮድካስቲንግ ሚዲያ፣ በምርት ሌቭሊንግ፣ የህትመት ሚዲያ) ዓይነት የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤
7. በየደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት፤
8. በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ ከ21-25% የተጣራ ትርፍ መጠን መሆን አለበት፤

9. ካለው የማምረት አቅም 60% እና በላይ ያመረተ፤
10. ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ዘመናዊ የሥራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፤
11. ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ምርት ማምረት አለበት፤
12. ከአምራች ኢንዱስትሪው አባላት ወይም ቋሚ ሰራተኞች መካከል ቢያንስ 25% የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው::

44. <u>በተቋማዊ አደረጃጀትና አመራር</u>

1. ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ መሆን አለበት፤
2. ለተሰማራበት ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት እና ዓመታዊ ኦዲት ማስደረግ አለበት፤
3. የማምረቻ ማዕከል አደረጃጃት የምርት ሂደትን የተከተለና ንጽህናው የተጠበቀ መሆን አለበት፤
4. የአባላትን እና የሠራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እንዲሁም እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የሥራ ላይ የደህንነት መሣሪያዎች እና የመሳሰሉት የተሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፤
5. ሥራውን ለማስፋፋት የሚያስችል በፅሁፍ የተዘጋጀ የንግድ ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት፤
6. ከሌሎች አምራች እና አቅራቢ ተቋማት ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የቢዝነስ ግንኙነት መፍጠር አለበት።

45. <u>የሚሰጡ ድጋፎች አጠቃቀም</u>

1. የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሙሉ ማዕቀፎች ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራር ተሞክሮውን ለሌሎች ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በክትትልና ድጋፍ የተረጋገጠ፤
2. የአምራች ኢንዱስትሪ ባለቤት እና ሰራተኛ ከክህሎት ስልጠና ተቋም ጋር በትብብር እና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የሚሳተፍ፤
3. ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ከሆነ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት፤

4. የማምረቻና መሸጫ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለበትና ከማዕከሉ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆን አለበት፤

5. የተፈጠረለትን የገበያ ትስስር ወይም ዕድሉን በአግባቡ የሚጠቀም መሆን አለበት፡፡

46.<u>በቴክኖሎጂ አጠቃቀም</u>

1. አምራች ኢንዱስትሪው ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት፤

2. የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት፤

3. በአምራች ኢንዱትሪው በራሱ አቅም የተሻሻለ የምርት ቴክኖሎጂ ቢያንስ አንድ መኖር አለበት፡፡

47.<u>ኃላፊነት ስለመወጣት</u>

1. አምራች ኢንዱስትሪው የሚጠበቅበትን ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፤
2. አምራች ኢንዱስትሪው ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፤
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የሚጠበቅበት አምራች ኢንዱስትሪዎች የተመዘገበ መሆን አለበት፤
4. አምራች ኢንዱስትሪው የማምረት ሂደት ወይም የአገልግሎት አቅርቦት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆን አለበት፤
5. ማህበራዊ ኃላፊነት ላይ መሳተፍ አለበት፡፡

48.<u>የሃገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ስለመጠቀም</u>

አምራች ኢንዱስትሪው ከሚጠቀማቸው የጥሬ ዕቃ መካከል በሃገር ውስጥ የሚመረት ከሆነ ቢያንስ 20 በመቶ የሚሆነውን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከሃገር ውስጥ መጠቀም አለበት፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች</u>

49.<u>በሥራ እድል ፈጠራ በሃብት፣ በገበያ፣ በትርፋማትና በምርታማነት መጠን</u>

1. የአምራች ኢንዱስትሪው ባለቤትን ፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ101 ሰዎች በላይ ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን አለበት፤
2. ጠቅላላ የሀብት መጠን ከብር 90,000,001 (ብር ዘጠና ሚሊዮን አንድ) በላይ መሆን አለበት፤
3. በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሃብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሃብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤
4. ከጠቅላላ ሃብቱ ውስጥ 50% እና በላይ ለቋሚ ንብረት ያዋለው መሆን አለበት፤
5. ዓመታዊ የግብይት ሽያጭ መጠን ከብር 90,000,000 በላይ መሆን አለበት፤
6. ምርትና አገለልግሎቱን ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት (ኢ-ኮሜርስ፣ በብሮድካስቲንግ ሚዲያ፣ በምርት ሌቭሊንግ፣ በህትመት ሚዲያ) ዓይነት የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤
7. በየደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት፤
8. በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ ከ21-25% የተጣራ ትርፍ መጠን መሆን አለበት፤
9. ካለው የማምረት አቅም 60% እና በላይ ያመረተ መሆን አለበት፡፡
10. ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ዘመናዊ የሥራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፤
11. ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ምርት ማምረት አለበት፤
12. ከአምራች ኢንዱስትሪው አባላት ወይም ቋሚ ሰራተኞች መካከል ቢያንስ 25% የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኑ መሆን አለባቸው::

50. <u>በተቋማዊ አደረጃጀትና አመራር</u>

1. ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ መሆን አለበት፤
2. ለተሰማራበት ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርአት መዘርጋት እና ዓመታዊ ኦዲት ማስደረግ አለበት፤
3. የማምረቻ ማዕከል አደረጃጃት የምርት ሂደትን የተከተለና ንጽህናው የተጠበቀ መሆን አለበት፤
4. የአባላትን እና ሰራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እንዲሁም እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የሥራ ላይ የደህንነት መሣሪያዎች እና የመሳሰሉት የተሟሉ

መሆን ይኖርባቸዋል፤

5. ሥራውን ለማስፋፋት የሚያስችል በፅሁፍ የተዘጋጀ የንግድ ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት፤
6. ከሌሎች አምራች እና አቅራቢ ተቋማት ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የቢዝነስ ግንኙነት መፍጠር አለበት::

51.<u>የሚሰጡ ድጋፎች አጠቃቀም</u>

1. የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሙሉ ማዕቀፎች ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራር ተሞክሮውን ለሌሎች ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በክትትልና ድጋፍ የተረጋገጠ፤
2. የአምራች ኢንዱስትሪ ባለቤት እና ሰራተኛ ከክህሎት ስልጠና ተቋም ጋር በትብብር እና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የሚሳተፍ፤
3. ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ከሆነ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት፤
4. የማምረቻና መሸጫ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለበትና ከማዕከሉ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆን አለበት፤
5. የተፈጠረለትን የገበያ ትስስር ወይም ዕድሉን በአግባቡ የሚጠቀም፡፡

52.<u>በቴክኖሎጂ አጠቃቀም</u>

1. አምራች ኢንዱስትሪው ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት፤
2. የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት፤
3. በአምራች ኢንዱትሪው በራሱ አቅም የተሻሻለ ቢያንስ ሁለት የምርት ቴክኖሎጂ መኖር አለበት፡፡

53.<u>ኃላፊነት ስለመወጣት</u>

1. አምራች ኢንዱስትሪው የሚጠበቅበትን ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፤
2. አምራች ኢንዱስትሪው ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፤
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የሚጠበቅባቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፤

4. አምራች ኢንዱስትሪው የማምረት ሂደት ወይም የአገልግሎት አቅርቦት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆን አለበት፤
5. ማህበራዊ ኃላፊነት ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡

54.<u>የሃገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ስለመጠቀም</u>

አምራች ኢንዱስትሪው ከሚጠቀማቸው የጥሬ ዕቃ መካከል በሃገር ውስጥ የሚመረት ከሆነ 20 በመቶ የሚሆነውን የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከሃገር ውስጥ መጠቀም አለበት፡፡

55.<u>ስለ ተጨማሪ የዕድገት ደረጃ ሽግግር መመዘኛ</u>

በክፍል ስምንት እና ዘጠኝ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ በአባሪ 4 የተገለጹት ዝርዝር የአምራች ኢንዱስትሪዎች የዕድገት ደረጃ ሽግግር መመዘኛ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

56.<u>ስለ እድገት ደረጃ ሽግግር አወሳሰን</u>

1. በክፍለ ከተማ ደረጃ የእድገት ደረጃ ሰርትፊኬት የሚያስፈልጋቸውን ወይም ያመለከቱ፡ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የእድገት ደረጃ የሚሸጋገሩ አምራች ኢንዱትሪዎችን መረጃ በማደራጀትና በጽህፈት ቤቱ ፕሮሰስ ካውንስል በማጸደቅ ለቢሮው ይልካል፤ በማዕከል የሚመለከተው የዘርፍ ፕሮሰስ ካውንስል የተላከለትን ገምግሞና አጽድቆ ሪፖርቱን ለቢሮው ያቀርባል፤
2. በቢሮ ደረጃ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የሚሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መረጃ በማደራጀት የሚመለከተው የቢሮው የዘርፉ ፕሮሰስ ካውንስል ገምግሞ ሪፖርት ለቢሮው ስትራቴጂክ ካውንስል በማቅረብ የእድገት ደረጃ ሰርትፊኬት እንዲሰጣቸው ያስወስናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የእድገት ደረጃ ሰርተፍኬት በከተማ ደረጃ የሚሰጥ ይሆናል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእድገት ደረጃ አፈጻጸም የሚቀርብ ቅሬታ ካለ በከተማ በሚዋቀር ቡድን ተጣርቶ ሲቀርብ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

57.<u>ስለ ማምረት አቅም ልኬት</u>

1. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ በዓመት ሁለት ጊዜ የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት እንዲለካ ይደረጋል፤

2. ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት በሚደረግበት ወቅት ጥራት ያለው አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ፣ የማስለካት እና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

58.ስለ መረጃ እና ድጋፍና ክትትል

1. የሥራና ክህሎት ቢሮ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መረጃን በሚያስቀምጠው የሽግግር አሰራር ሥርዓት መሰረት ለኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ መረጃዎችን አጠናክሮ በሶፍት ኮፒ እና በሃርድ ኮፒ ይልካል፤
2. የስራና ክህሎት ቢሮ የላከውን መረጃ የቢሮው የእድገት ደረጃና ሽግግር ዳይሬክቶሬት ለአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 526/2015 በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት ትክክለኛነቱን በማረጋገት የመረከብ ሥራዎችን ይሰራል፤
3. በመመሪያ የተቀመጡ አሰራሮችን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍና ክትትል ማኑዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፤
4. ቢሮው ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጣቸው መንግስታዊ፣ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፎችን ለማከናወን የሚያስችለውን የድጋፍና ክትትል ማኑዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

59. በቅንጅት ስለመስራት

ቢሮው የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፤ ለማዘመን፣ ሀገር በቀል እና የማምረቻ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙና እዲሻሻሉ ለማስቻል እና የኢንዱስትሪዎቹን የእድገት ደረጃ ሽግግር ለማፋጠን ከከፍተኛ የትምህርት፣ ከጥናትና ምርምር እና ከፋይናንስ አቅራቢና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በጋራ፣ በቅንጅትና በትብብር የሚሰራበት አሰራር ይዘረጋል፤ ተቋማቶቹ የሚያወጧቸው አሰራሮች እና የህግ ማእቀፎችንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

60. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

61.<u>ስለ ተጠያቂነት</u>

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

62.<u>የተሻረ ሕግ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች</u>

1. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የአገልግሎት እና ድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ቁጥር 152/2016 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ቢሮው ያወጣው መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

63.<u>መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ -2017 ዓ.ም**

**ጃንጥራር አባይ ይግዛው**

**የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ እና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ**

## አባሪ 1

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ ወይም ኤክስፖርት የሚያደርጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች አዲስ የመስሪያ ቦታ፣ የማስፋፊያ እና ማምረት ጀምረው የመሬት ድጋፍ አገልግሎት የሚጠይቁ ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና ክላስተር ማዕከላት ሊገቡ የሚችሉ ለመለየት የተዘጋጀ መመልመያ መስፈርት፡-

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርት | የተሰጠ ክብደት ከመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ደረጃውን የጠበቀ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማቅረብ፤ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 2 | የሚቀርበው ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ካለው የመስሪያ ቦታ ጋር የሚጣጣም መሆኑ፤ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 3 | የዕድገት ደረጃው አነስተኛና ከዚያ በላይ የሆነ፤ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 4 | ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው እና የሚጠበቅበትን ግብር የከፈለ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 5 | በወቅቱ በስራ ላይ እያለ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል፤ | 22 | |
| 6 | ምርታቸውን ወደ ውጪ የሚልኩ፤ | 48 | |
| 7 | የማምረት አቅም አጠቃቀም የተሻለ ከሆነ፤ | 25 | |
| 8 | በማህበራዊ ተሳትፎ በተጨባጭ የሚሳተፍ ከሆነ፤ | 5 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 100 | |

**ማብራሪያ**

- ተወዳዳሪ አምራች ኢንዱስትሪ የሚወዳደሩት በስትራተጂክ ተኪ ምርት ከሆነ በዚሁ የተመላከተው ተጥብ የሚያዝ ይሆናል፤
- የኤክስፖርት ምርት/ምርታቸውን ወደ ውጪ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ሙሉ ነጥብ የሚያገኘው ንግድ ፍቃድ ያለው፣ ወደ ውጪ ምርቱን ስለመላኩ በምርት መጠንና ባስገኘው የውጪ ምንዛሬ ገቢ መጠን ህጋዊ ማስረጃ

ማቅረብ ሲችል፤

- ተኪ ምርት እና ኤክስፖርት የሚያመርት ተወዳዳሪ አምራች ኢንዱስትሪ ሁለቱንም ነጥብ በመደመር አማካኝ ተሰልቶ ውጤቱ የሚያዝ ይሆናል፤
  ለምሳሌ፡- የተኪ ምርት ነጥብ ያገኘው 40 ቢሆን እና በኤክስፖርት ደግሞ 42 ነጥብ ቢያገኝ አማካኝ ውጤቱ እንደሚከተለው ይሰላል፡-

$$\text{በአማካኝ የተገኘ ውጤት} = \frac{\text{በተኪ ምርት የተገኘ ነጥብ} + \text{በኤክስፖርት የተገኘ ነጥብ}}{2}$$

$$\text{በአማካኝ የተገኘ ውጤት} = \frac{40+42}{2} = 41$$

- የማምረት አቅም አጠቃቀም በተመለከተ ቢሮው በበጀት ዓመቱ በከተማ ደረጃ የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት መጠን በሚያስቀምጠው ግብ መሰረት ግቡን ያሚላ አምራች ኢንዱስትሪ 25% ያገኛል፡፡ በዚሁ ስሌት መሰረት የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም አጠቃቀም ሲለካ ቢሮው ካስቀመጠው የበጀት ዓመቱ የማምረት አቅም አጠቃቀም ግብ በታች ሲሆን ከመቶው ተሰልቶ ነጥብ ይቀመጣል፤
- ማንኛውም አምራች ኢንዱስትሪ በማህበራዊ ተሳትፎ ስላለው ድርሻ በሚሰጠው ነጥብ ላይ ከአስተዳደሩ ወይም ከፌደራል መንግስት ወይም ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም ማህበራዊ ተሳትፎ ስለማድረጉ የሚገልጽ ደብዳቤ ወይም ሠርተፍኬት ወይም ሁለቱንም ሲያቀርብ ሙሉ ነጥብ ያገኛል፡፡ በአንጻሩ ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ ካልቻለ በዚህ ረገድ ነጥብ አይሰጠውም፤
- በሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱት ማንኛውንም ዓይነት ምርቶች እንደ ተኪ ምርት ተወስደው በመስፈርቱ የተቀመጠውን ነጥብ ያገኛሉ፡፡

## አባሪ 2

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

ተኪ-ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች አዲስ የመስሪያ ቦታ፣ የማስፋፊያ እና ማምረት ጀምረው የመሬት ድጋፍ አገልግሎት የሚጠይቁ ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና ክላስተር ማዕከላት ሊገቡ የሚችሉ ለመለየት የተዘጋጀ መመልመያ መስፈርት፡-

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርት | የተሰጠ ክብደት ከመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 2 | የዕድገት ደረጃ ሰርትፍኬት | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 3 | የሚጠበቅበትን የወቅቱን ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርብ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 4 | በወቅቱ በስራ ላይ እያለ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል፤ | 22 | |
| 5 | ተኪ ምርት የሚያመርት የሚያደርግ ከሆነ | 48 | |
| 6 | ማህበራዊ ተሳትፎ | 5 | |
| 7 | የማምረት አቅም አጠቃቀም የተሻለ ከሆነ፤ | 25 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **100** | |

ማብራሪያ

- የተኪ ምርት አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ሙሉ ነጥብ የሚያገኘው በኢንዱስትሪ ሚኒስትር የተኪ ምርት ስትራቴጅ ላይ የተዘረዘሩ ምርቶችን የሚያመርት ከሆነ፣ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው የአሰራር ማኑዋል መሰረት ይሆናል፤
- ተኪ ምርት እና ኤክስፖርት የሚያመርት ተወዳዳሪ አምራች ኢንዱስትሪ ሁለቱንም ነጥብ በመደመር አማካኝ (avarege) ተሰልቶ ውጤቱ የሚያዝ ይሆናል፤

  ምሳሌ፡- የተኪ ምርት ነጥብ ያገኘው 45 ቢሆን እና በኤክስፖርት ደግሞ 32 ነጥብ

ቢያገኝ አማካኝ ውጤቱ እንደሚከተለው ይሰላል፤

$$በአማካኝ\ የተገኘ\ ውጤት = \frac{በተኪ\ ምርት\ የተገኘ\ ነጥብ + በኤክስፖርት\ የተገኘ\ ነጥብ}{2}$$

$$በአማካኝ\ የተገኘ\ ውጤት = \frac{45+32}{2} = \underline{\underline{38.5}}$$

- የማምረት አቅም አጠቃቀም በተመለከተ ቢሮው በበጀት ዓመቱ በከተማ ደረጃ የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት መጠን በሚያስቀምጠው ግብ መሰረት ግቡን ያሟላ አምራች ኢንዱስትሪ 25% ያገኛል፡፡ በዚሁ ስሌት መሰረት የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም አጠቃቀም ሲለካ ቢሮው ካስቀመጠው የበጀት ዓመቱ የማምረት አቅም አጠቃቀም ግብ በታች ሲሆን ከመቶው ተሰልቶ ነጥብ ይቀመጣል፡፡
- አንድ አምራች ኢንዱስትሪ በማህበራዊ ተሳትፎ ስላለው ድርሻ በሚሰጠው ነጥብ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ በየደረጃው ከሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች በአንዱ ወይንም ከፌደራል መንግስት ወይንም ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም ማህበራዊ ተሳትፎ ስለማድረጉ የሚገልጽ ደብዳቤ ወይንም ሠርተፍኬት ወይንም ሁለቱንም ሲያቀርብ ነጥብ ይሰጠዋል፡፡ በአንጻሩ ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ ካልቻለ በዚህ ረገድ ነጥብ አይሰጠውም፡፡
- በሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱት ማንኛውንም ዓይነት ምርቶች እንደ ተኪ ምርት ተወስደው በመስፈርቱ የተቀመጠውን ነጥብ ያገኛሉ፡፡

## አባሪ 3

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር ድጋፍ ፍላጎት መመልመያ መስፈርት

| ተ.ቁ | መመዘኛ መስፈርት | የተሰጠ ክብደት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለው | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 2 | የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ያለው | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 3 | የወቅቱን ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ የሚያቀርብ | ቅድመ ሁኔታ/ግዴታ ነው | |
| 4 | የፈጠረው ቋሚ ስራ ዕድል በፔሮል መረጃ የሚያቀርብ | 22 | |
| 5 | ተኪ ምርት የሚያመርት ከሆነ | 23 | |
| 6 | ኤክስፖርት የሚያደርግ ከሆነ | 25 | |
| 7 | ማህበራዊ ተሳትፎ | 5 | |
| 8 | የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት ያስለካ | 25 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 100 | |

# አባሪ 4

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ካይዘን ትግበራ የፍተሻ እና መመዘኛ ነጥቦች

**የ5ቱ ማ ውጤት መለክያ ቅፅ (1)**

| የተለካበት ቀን: | የለካው ሰው ስም: |
|---|---|
| | |

የውጤት መመዘኛ

*ደረጃ 5*: **በጣም ጥሩ** (ምንም ዓይነት ችግር የለም)

*ደረጃ 4*: **ጥሩ** (በስራ ቦታ ደረጃ ጥሩ ነው ምንም እንኳ አንዳንድ እቃዎች ላይ ችግር ቢኖርም)

*ደረጃ 3*: **መካከለኛ** (በስራ ቦታ ደረጃ ደህና ነው ምንም እንኳ አንዳንድ እቃዎች ላይ ችግር ቢኖርም)

*ደረጃ 2*: **ደካማ** (ብዙ ቦታዎች ላይ ሊሻሻሉ የሚችሉ ችግሮች ይታያሉ)

*ደረጃ 1*: **መጥፎ** (ብዙ ቦታዎች ላይ መሻሻል ያለባቸው ትላልቅ ችግሮች ይታያሉ)

| ጠቅላላ የምዘናው ውጤት |
|---|
| ①+②+③+④+⑤+⑥=[ ] |
| የ5ቱ ማ ውጤት= (ጠቅላላ ነጥብ÷200) ×100 =[ ] % Max.100% |

| | Check Items (የመለክያ ነጥቦች) | የምዘናው ውጤት 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | አማካይ | የምዘናው ውጤት 2 እና ከዛ በታች ከሆነ አስተያየትዎ ይፃፉ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስራ ቦታ | በጠረጴዛ፣ መደርደሪያና መሬት ላይ የተቀመጡ ወይም የተጣሉ አላስፈላጊ ነገሮች ስላለመኖራቸው | | | | | | ① | |
| | እቃዎች ስራ በሚረብሽ ሁኔታ ስላለመቀመጣቸው እንዲሁም አቀማመጣቸው መጨናነቅ ስላለመፍጠሩ | | | | | | | |
| | አሁን ባለበት ሁኔታ እቃዎች ከተቀመጡበት ስላለመውደቃቸው | | | | | | | |
| | እቃዎች ከእሳት አደጋ መከላከያ እና ከመብራት ማጥፊያና ማብሪያ አጠገብ ወይም ፊት ለፊት ስላለመቀመጣቸው | | | | | | | |

| | Check Items (የመለከያ ነጥቦች) | የምዘናው ውጤት | | | | | አማካይ | የምዘናው ውጤት 2 እና ከዛ በታች ከሆነ አስተያየትዎ ይፃፉ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| | ምንም የወዳደቀ ቆሻሻ ይሁን ብክነት ስላለመኖሩ | | | | | | | |
| | ማፅዳት እንዲሁም ደግሞ ፅዳት በቀጣይነት ስለመተግበሩ | | | | | | | |
| | መሬቱ ወይም የስራ ቦታው በውሃ እና በዘይት ምክንያት ስላለመበላሸቱ | | | | | | | |
| መራጃዎች (tools | መራጃዎች (tools) በፍጥነት መጠቀም ስለመቻል | | | | | | ② | |
| | መራጃዎች (tools) ላይ ምንም ዓይነት የጉዳትና የቆሻሻ ችግር ስላለመኖሩ | | | | | | | |
| | አላስፈላጊ መራጃዎች (tools) ስላለመቀመጣቸው | | | | | | | |
| | እያንዳንዱ መራጃዎች (tools) የሚቀመጡበት ቦታ በግልፅ ስለመታወቁ | | | | | | | |
| | የተጠቀምንበት ወይም የተገለገልንበት መራጃ ወደ ቦታው ስለመመለሱ | | | | | | | |
| | መራጃዎች (tools) ሽልፍ ላይ በተዘጋጀላቸው ቦታ በስነስርዐት ስለመቀመጣቸው | | | | | | | |

| | Check Items (የመለከያ ነጥቦች) | Not Good ⇔ good | | | | | አማካይ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| ማሽኖችና መገልገያ ዕቃዎች | ለግል የምንጠቀምባቸው እና ለጋራ የምንጠቀምባቸው እቃዎች ተለይተው ስለመቀመጣቸው | | | | | | | |
| | ለጋራ የምንጠቀምባቸው እቃዎች የሚቀመጡበት ቦታ እና መመሪያ ግልፅ ስለመሆኑ (ስንጠቀምበት) | | | | | | | |
| | በዓይነት እንዲሁም በብዛት አላስፈላጊ ወይም ከመጠን በላይ የሆኑ እቃዎች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | ማሽኖችና መገልገያ እቃዎችን በቶሎ ማግኘት ስለመቻሉ | | | | | | | |
| | የጥበቃ እንዲሁም ደግሞ የጥገና ሀላፊነት የተሰጠው ሰው ተወስኖ ስለመታወቁ | | | | | | ③ | |
| | ማሽኖችና መገልገያ እቃዎች ከተጠቀምንባቸው በኋላ ወደ ቦታቸው ስለመመለሳቸው | | | | | | | |
| | ማሽኖችና መገልገያ እቃዎች በንፅህና ስለመያዛቸው | | | | | | | |
| አመላካችና ጠቋሚ | ግድግዳ ላይ ጊዜ ያለፈባቸው እና የማያገለግሉ ፖስተሮችና ማስታወቂያዎች ስላለመኖራቸው | | | | | | ④ | |
| | በቆሻሻና በተለያዩ ነገሮች ተጋርደው ለማንበብ አስቸጋሪ የሆኑ መልዕክት አስተላላፊ ፅሁፎች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |

| | Check Items (የመለክያ ነጥቦች) | Not Good ⇔ good | | | | | አማካይ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| | የመስርያ ቦታ ይዘትና አመላካቾቻቸው ስለመጣጣማቸው | | | | | | | |
| | መተላለፍያ መንገድ (walk way) እና መስርያ ቦታ የሚለዩበት መስመር ስለመኖሩ | | | | | | | |
| | የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች የተቀመጡት የእሳት አደጋን በሚያመጡት ስፍራዎች ስለመሆኑ | | | | | | | |
| መተላለፍያ መንገድ(walk way) | መተላለፍያ መንገዶች (walk way) በነጭ(በሌላ ቀለም) መስመር የደመቁ ስለመሆናቸው | | | | | | ⑤ | |
| | መተላለፍያ መንገድ (walk way)ላይ የተቀመጡ ነገሮች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | ሊያደናቅፉ ወይም ሊያንሸራትቱ የሚችሉ አደገኛ ነገሮች በመተላለፊያ መንገዶች ላይ ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | መተላለፍያ መንገዶችን (walk way) አስፈላጊ የሆነ አመላካች ስለመኖሩ | | | | | | | |
| ማከማቻ | የክምችቶች አያያዝ እና የማከማቻ ቦታዎች በቀላሉ መታወቃቸው | | | | | | ⑥ | |
| | የተከማቹ ንብረቶች የአገልግሎት ጊዜ ማብቂያ በግልፅ ስለመቀመጡ | | | | | | | |
| | የክምችት ክፍል ለማስተዳደር ሀላፊነት የተሰጠው ሰው ስለመወሰኑ | | | | | | | |
| | ያቀማመጥ ሁኔታዉ የተቀመጡ ነገሮችን በፍጥነት ለማግኘትና ለመጠቀም የሚመች ስለመሆኑ | | | | | | | |
| | መቀመጫ ቦታቸው ባለመወሰኑ የተበታተኑ እቃዎች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | መንገዶች(walk way) ላይና መደርደሪያዎች አካባቢ የተቀመጡ እቃዎች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | የማያስፈልጉ ነገሮችን በጥንቃቄ ለይቶ ማስወገድን በተመለከተ | | | | | | | |
| | የማከማቻ ቤት መገልገልገያ መሳሪያዎች ለምሳሌ መደርደርያ፣ጠረጴዛና መወጣጫ መሰላሎች ምንም ያልተበላሹ ስለመሆናቸው | | | | | | | |
| | የተለያዩ ቁሳቁሶች ተደበላልቀው ስላለመቀመጣቸው | | | | | | | |
| | ምን እንደተከማቸ በግልፅ መታወቃቸውን በተመለከተ | | | | | | | |
| | የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ንብረቶች ስላለመኖራቸው | | | | | | | |
| | የተከማቹ እቃዎችን የማጣራት እና ያለቁ እቃዎችን የመተካት ሀላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ተለይተው ስለመታወቃቸው | | | | | | | |

## አባሪ 5

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች የካይዘን ትግበራ ድጋፍ ፍላጎት መመልመያ መስፈርት

| ተ.ቁ | ለካይዘን ትግበራ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መመልመያ መስፈርት ነጥብ መስጫ ቅጽ | | | | | | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥቅል ትኩረቶች | የሚረጋገጡ ነጥቦች | የሚሰጥ ነጥብ | | | | |
| | | | 0 | 1 | 2 | 3 | |
| 1 | ጥራት | የጥራት ቁጥጥር ስርዓት መኖሩ | | | | | |
| | | የተጠና የጥራት ጉድለት ልኬት (በመቶኛ) | | | | | |
| | | የጥራት ችግሮች መንስኤዎቻቸው ተለይተው መታወቅ/ አለመታወቃቸው፤ | | | | | |
| | | የስራ አካባቢው አደረጃጀት እና የስራ ሂደት ፍሰት በጥራት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ መኖር አለመኖሩ፤ | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር፡-** | | | | | |
| 2 | ምርታማነት | ኩባንያው በዕቅድ የያለው የምርት አቅም እና አሁን የደረሰበት ደረጃ | | | | | |
| | | የማሽነሪዎች ሙሉ አቅም እና አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለ አቅም (ለናሙና በተመረጡ ዋና ዋና ማሽኖች ብቻ) | | | | | |
| | | የግብዓት አጠቃቀም ውጤታማነት (በዕቅድ እና ነባራዊ ሁኔታ መካከል ያለ ልዩነት | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር፡** | | | | | |
| 3 | ደህንነት | የስራ አካባቢው አደረጃጀት በምርታማነት ላይ እያሳደረ ስላለው ተፅዕኖ | | | | | |
| | | ደህንነት ስጋት የሚሆኑ ስራዎች መኖር/አመኖራቸው | | | | | |
| | | የደህንነት መርጃ መሳሪያዎች ስለመቅረባቸው እና የሰራተኞች የአጠቃቀም ውጤታማነት | | | | | |
| | | የስራ አከባቢው አደረጃጀት ከደህንነት ስጋት የፀዳ መሆን/አለመሆኑ | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር፡-** | | | | | |
| 4 | ፍላጎት እና ቁርጠኝነት | በሚላከው ፎርም/ቅጽ ላይ የሚሰጡት የአዎንታ ምላሽ | | | | | |
| | | በአምራች ኢንዱስትሪው ቅደመ ዳሰሳ ወቅት የበላይ አመራሩ ለስራው መቃናት | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር፡-** | | | | | |
| 5 | ገቢ ምርት የሚተኩ | የሚመረተው የምርት ዓይነት ጥራት | | | | | |
| | | የሚያስቀሩት ወጪ | | | | | |
| | | የምርት ብዛት | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር፡-** | | | | | |
| 6 | የሠራተኛ | አጠቃላይ የሠራተኛ ብዛት | | | | | |

| ተ.ቁ | ለካይዘን ትግበራ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መመልመያ መስፈርት ነጥብ መስጫ ቅጽ | | | | | | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥቅል ትኩረቶች | የሚረጋገጡ ነጥቦች | የሚሰጥ ነጥብ | | | | |
| | | | 0 | 1 | 2 | 3 | |
| | ብዚት | ቋሚ እና ጊዜያዊ የሠራተኛ ብዛት | | | | | |
| | | የወንድ እና ሴት ሠራተኛ ብዛት | | | | | |
| | | አጠቃላይ ድምር፡- | | | | | |
| 7 | የብቃት ሠርተፍኬት | የተተገበሩ የለውጥ መሳሪያዎች ብዛት | | | | | |
| | | የተያዘ የትግበራው ማሳያ መረጃዎች | | | | | |
| | | አጠቃላይ ድምር፡- | | | | | |
| 8 | የደንበኛ ቅሬታ | የቅሬታ መቀበያ ሥርዓት መኖሩ | | | | | |
| | | የተመደበ የደንበኛ ቅሬታ በመቶኛ | | | | | |
| | | አጠቃላይ ድምር፡- | | | | | |
| 9 | ኤክስፖርት የሚያደርጉ | ወደ ውጭ የሚላከው የምርት ዓይነት | | | | | |
| | | የሚላከው ምርት መጠን በፐርሰንት | | | | | |
| | | አጠቃላይ ድምር፡- | | | | | |
| 10 | ሌሎች/አማካሪ የሚሞላው | የሥራው ቦታው በአግባቡ መደራጀቱ | | | | | |

**ለካይዘን ትግበራ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መመልመያ መስፈርቶች የተቀመጠ ክብደት**

| ተ.ቁ | ኩባንያ መለያ መስፈርች | የተሰጠው ክብደት በመቶኛ |
|---|---|---|
| 1 | የምርት ጥራት ሁኔታ | 10 |
| 2 | የምርታማነት ሁኔታ | 10 |
| 3 | የደህንነት ሁኔታ | 10 |
| 4 | ፍላጎት እና ቁርጠኝነት | 10 |
| 5 | የገቢ ምርት የሚተኩ | 10 |
| 6 | የሠራተኛ ብዛት | 10 |
| 7 | የብቃት ሠርተፍኬት | 5 |
| 8 | የደንበኛ ቅሬታ | 10 |
| 9 | ኤክስፖርት የሚያደርጉ መሆናቸው | 15 |
| 10 | ሌሎች/የአማካሪ ምልከታ | 10 |
| ድምር | | 100 |

**<u>ማብራሪያ</u>፡-** ከላይ የተዘረዘሩት አራቱ መስፈርቶች በጥቅል መቀመጣቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአራቱም መስፈርት ስር የተዘረዘሩት ነጥቦች የሚለኩበት ሁኔታ እንደሚከተለው ይሆናል፤

- ሙሉ ለሙሉ ያልተገበረ ዜሮ ነጥብ፣
- በአነስተኛ ደረጃ የተገበረ አንድ ነጥብ፣
- በመካከለኛ ደረጃ የተገበረ ሁለት ነጥብ፣
- ሙሉ ለሙሉ የተገበረ ሶስት ነጥብ ያገኛል፡፡

## አባሪ 6

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር መስፈርቶችና መመዘኛ ነጥቦች

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ደረጃዎች አንፃር ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ/%/ | | | መስፈርቶቹ የሚለኩባቸው ስልቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ አነስተኛ | ወደ መካከለኛ | ወደ ከፍተኛ | |
| **1** | **ሥራ ዕድል ፈጠራ** | **20** | **25** | **25** | ፔይ ሮልን መነሻ በማድረግ በቁጥር |
| 1.1 | ቋሚ የሥራ ዕድል | 15 | 20 | 20 | |
| 1.2 | ጊዜያዊ የሥራ ዕድል | 5 | 5 | 5 | |
| **2** | **የሀብት መጠን** | **30** | **35** | **35** | የተረጋጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ መግለጫ |
| 2.1 | ጠቅላለ የሀብት መጠን | 15 | 15 | 20 | |
| 2.2 | በብድር ከተገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለ መጠን | 15 | 20 | 15 | |
| **3** | **ትርፋማነት** | **15** | **10** | **10** | የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ ፣ የሀብትና ዕዳ መግለጫ የትርፍና ኪሰራ መግለጫ |
| 3.1 | ተከታታይና ተመጣጣኝ ትርፍ ማስመዝገብ | 5 | 3 | 5 | |
| 3.2 | ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋት እና ወይም ለቁጠባ የዋለ ገንዘብ መጠን | 10 | 7 | 5 | |
| **4** | **የገበያ መጠን** | **8** | **8** | **10** | |
| 4.1 | ዓመታዊ የሽያጭ መጠን | 2 | 2 | 3 | የሽያጭ መረጃ በማየት |
| 4.2 | ከመንግስት ውጪ የተፈጠረ የገበያ ትስስር መጠን | 2 | 3 | 2 | የሽያጭ መረጃ በማየት |

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ደረጃዎች አንፃር ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ/%/ | | | መስፈርቶቹ የሚለኩባቸው ስልቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ አነስተኛ | ወደ መካከለኛ | ወደ ከፍተኛ | |
| 4.3 | በንዑስ ኮንትራት ለሌሎች ኢንተርፕራይዞች በዓመት የፈጠረው የገበያ ትስስር ብዛት | 2 | 1 | 3 | ውል በማየት |
| 4.4 | ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች | 1 | 1 | 1 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 4.5 | የኤግዚቪሽንና ባዛር ተሳትፎ ብዛት | 1 | 1 | 1 | በተሳትፎ የምስክር ወረቀት |
| **5** | **ምርታማነት** | **7** | **4** | **5** | |
| 5.1 | ካለው ሙሉ የማምረት አቅም የተጠቀመ | 3 | 2 | 3 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት (የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት ውጤት) |
| 5.2 | የምርታማት ዕድገት ያስመዘገበ | 4 | 2 | 2 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት (ያደገ የምርታማነት ዕድገት መጠን ውጤት) |
| **6** | **በቢሮው የሚሰጡ ድጋፎች አጠቃቀም** | **4** | **4** | **4** | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 6.1 | ወቅቱን ጠብቆ የተሰጠውን ብድር (የካፒታል ሊዝና የስራ ማስኬጃ ብድር) የመመለስ ሂደት | 2 | 2 | 2 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት (ድጋፉን ከሚሰጡ ተቋማት የሚሰጥ ማረጋገጫ ደብዳቤ) |

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ደረጃዎች አንፃር ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ/%/ | | | መስፈርቶቹ የሚለኩባቸው ስልቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ አነስተኛ | ወደ መካከለኛ | ወደ ከፍተኛ | |
| 6.2 | የመንግስታዊ መስሪያ ቦታ አጠቃቀም | 1 | 1 | 1 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት (መስሪያ ቦታውን በአግባና የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ) |
| 6.3 | በቢሮው የሚሰጡ የሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፎችን በአግባቡ የተጠቀመ | 1 | 1 | 1 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት (የተሰጡትን ድጋፎች ተግባራዊ ያደረገ ) |
| 7 | **የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም** | 5 | 5 | 5 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 8 | **ተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት** | 5 | 4 | 3 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 9 | **ግዴታን ስለመወጣት** | 4 | 4 | 2 | ከአምራች ኢንዱስትሪው በሚገኝ መረጃ የሚሞላ |
| 9.1 | ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል | 2 | 3 | 1 | የገቢ ግብር ክሊራንስ |
| 9.2 | የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ማሳደስ | 2 | 1 | 1 | የታደሰ የምዝገባና የንግድ ፈቃድ |
| 10 | **የካይዘን ትግበራ** | 2 | 1 | 1 | ድጋፉን በሚያደርጉ የዘርፍ ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 10.1 | የመጀመሪያ ደረጃ ካይዘን ትግበራ (5ቱን "ማ" ዎችን ተግራዊ ያደረገ | 2 | 1 | 1 | |
| | **ድምር** | 100% | 100% | 100% | |

**ማስታወሻ፡-**

(1ኛ) የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር የሚፈፀመው ለየዕድገት ደረጃው በድምር በመቶኛ/%/ ከተቀመጠው ወደ አነስተኛ ≥ 75% ሲያገኙ& ወደ መካከለኛ ≥ 80% ሲያገኙ& እና ወደ ከፍተኛ ≥ 85% ሲያገኙ ይሆናል::

(2ኛ) ከላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን ከከፍተኛው ነጥብ ቀጥሎ ወደታች የሚገኝ የነጥብ ውጤት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ ስሌት በመስራት ይቀመጣል::

(3ኛ) የመንግስታዊ ድጋፎች ተጠቃሚ ያልሆነ አምራች ኢንዱስትሪ በዕድገት ደረጃ ሽግግር ወቅት ለዚህ የተቀመጠውን ሙሉ ነጥብ ያገኛል::

(4ኛ) ከተፈጠረው የስራ እድል ቋሚ /80%/ ጊዜያዊ /20%/ ታሳቢ በማድረግ የሚሰላ ይሆናል፡፡